# ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
# Federal Civil Service Commission

ቁጥር/Ref.No. ፌሲኮ30/ጠ13/25/18

ቀን/Date 21 2018

ለኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

<u>አዲስ አባበ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያን ስለመላክ</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ከየካቲት 12 ቀን 20012 ዓ.ም ጀምሮ ጸድቆ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ ተፈቅዶ የነበረው የቀን ውሎ አበል መጠን ከወቅቱ የገበያ ሁኔታ ጋር ለማጣጣምና መንግስት በቅርቡ ተግባራዊ እያደረገ ያለውን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርምን በላቀ ደረጃ ለማስፈጸም የመንግስት ሠራተኞችን የቀን ውሎ አበል ማሻሻያ እንዲደረግ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጥናቱ ለመንግስት ቀርቦ ተወስኗል፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ከመስከረም 1 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል የገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 20 ቀን 2018 ዓ.ም በቁጥር በበ18/6/134 በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡

ውሳኔውን ለማስፈጸም የተዘጋጀው የተሻሻለው የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የኮሚሽነሮች ጉባኤ ታይቶ ከመስከረም 1 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ የጸደቀ ሲሆን፣ በፍትህ ሚኒስቴርም ተልኮ መመሪያ ቁጥር 1111/2018 ተብሎ የተመዘገበና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ መጫኑን አስታውቀናል፡፡

ስልክ/Tel +251 11 554 96 66
011 554 96 67
011 554 96 68

ፋክስ/FAX +251 11 554 97 07
+251 11 554 96 63
ፖ.ሳ.ቁ/po.box-1082

ኢሜል/email-ethiocs@gmail.com
ዌብ ሳይት/website-www.csc.gov.et

አዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ከፍላሚንጎ ሬስቶራንት 100 ሜትር ገባ ብሎ

ማገልገል ክብር ነው!

ስለሆነም የተሻሻለው የቀን ውሎ አበል መጠን በፕሮግራም በጀት ከተያዘው ውጪ ተጨማሪ በጀት የማይፈቀድለት በመሆኑ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶችና የክልል ተቋማት በዚሁ አግባብ ሥራ ላይ እንዲያውሉት የተቋም የበላይ ኃላፊዎች፣ የኦዲት ባለሙያዎች ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ እያሳሰብን፣ የተዘጋጀውን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ከዚህ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ግልባጭ

ለገንዘብ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ለኮሚሽነር ጽ/ቤት

ለአደረጃጀት ብቃት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

ለክፍያና ጥቅማ ጥቅም መሪ ስራ አስፈጻሚ

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Federal Civil Service Commission

# የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1111/2018

መስከረም 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>**መግቢያ**</u>

በሥራ ላይ ያለው የመንግስት ሠራተኞች የቀን የውሎ አበል ተመን በስራ ላይ ከዋለ ከአሥራ ሁለት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በክልሎች፣ በዞንና በወረዳ ከተሞች የሚገኙ ሆቴሎች ከሚያስከፍሉት የምግብና የመኝታ ዋጋ ጋር ሊመጣጠን ባለመቻሉ ለመስክ ሥራ በሚወጡ ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ የወጪ ጫና በማሳደር በመስክ ስራ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳረፉም በላይ የሥራ ተነሳሽነትን በመቀነስ ለቅሬታና አቤቱታ ምክንያት በመሆኑ፣

በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (4) ጠፌፌራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአበል ዓይነቶችንና ክፍያዎችን እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል በሚል በመደንገጉ፣

በሌላ በኩል የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 502/2014 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 14 ብቃት ያላቸውን የስራ መሪዎችና ባለሞያዎችን ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶች ለመሳብና ለማቆየት የሚያስችል የክፍያ ሥርዓት እንዲኖር በየወቅቱ እያጠና ለመንግስት ውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል በሚል በመደንገጉ፣

ኮሚሽኑ በፌዴራል መንግስት ሰራኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 156 (2) መሰረት ለአፈጻጸም እንዲመች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ከሚሽን ይህን መመሪያ አውጥቷል።

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1118/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በመንግስት መሥሪያቤት ውስጥ የሚያገለግል ማንኛውም ሠራተኛና የሥራ ኃላፊ ነው፡፡
2. "የቀን ውሎ አበል" ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በአገር ውስጥ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ መመለስ ሳይችል ሲቀር ለአንድ ቀን የሚያስፈልገው የምግብና የመኝታ ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡
3. "የውሎ ገብ አበል" ማለት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ዕለቱን የሚመለስ ከሆና ለምግብ ለሚያወጣው ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡
4. "የአየር ፀባይ አበል" ማለት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ለመስክ ሥራ የአየር ፀባዩ አስቸጋሪ በመሆኑ የአየር ፀባይ አበል እንዲከፈል በመንግስት ተወስኖ ከመደበኛ ደመወዝ በተጨማሪ በየወሩ ለሰራተኞች በሙቶኛ እየተሰላ በሚከፈልባቸዉ ቦታዎች ሲንቀሳቀስ የሚከፈል አበል ነው፡፡

### 3. ዓላማ

ከሁን በስራ ላይ ያለውን የቀን ውሎ አበል መጠን ከወቅቱ ገበያ ጋር በማነጻጸርና በማሻሻል የመንግስት ሠራተኞች ለመስክ ስራ ተለሳሽነት እንዲኖራቸው እንዲሁም በመስክ ስራ ወቅት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡

### 4. የተፈጻሚነት ወሰን

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

ከመንግስት ተሿሚዎች በስተቀር ከፌደራል እስከ ቀበሌ አስተዳደር እርከን ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ በቋሚና ጊዜያዊነት ወይም በኮንትራት ተቀጥረው በሚያገለግሉ የመንግስት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 5. የጾታ አገላለጽ

በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

# ክፍል 2

# የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም

## 6. የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል

1. የቀን ውሎ አበል ተመን የሚሰላው ከአንድ ቀን የውሎ አበል ክፍያ ውስጥ ለቁርስ 10%፣ ለምሳ 25% ለእራት 25% እና ለአልጋ 40% በመመደብ ነው።
2. መንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል ሠራተኞችን በደመወዝ ደረጃቸው በሶስት እንደሚከተለው በመክፈል ይሆናል።
   ሀ/ ደረጃ አንድ፡- ከብር 6000 እስከ ብር 12499 ድረስ ላሉ የደመወዝ መጠኖች፣
   ለ/ ደረጃ ሁለት፡- ከብር 12500 እስከ 17999 ድረስ ላሉ የደመወዝ መጠኖች፣
   ሐ/ ደረጃ ሶስት፡- ከብር 18000 እና በላይ ላሉ የደመወዝ መጠኖች፣
3. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ መመለስ ካልቻለ ለሥራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልል፣ የዞንና የወረዳ ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንደንዱ ቀን በደመወዝ መጠናቸው መሰረት በዚህ መመሪያ ከሠንጠረዥ አንድ እስከ ሶስት በተመለከተው መሠረት ይከፈላል፤
   ሀ) ለክልል ዋና ከተማ የተመደበው ከታች በሠንጠረዥ 1 የተመለከተውን፣

ሠንጠረዥ 1: **የክልል ዋና ከተሞችና ከተሞች የአበል መጠን**

| ተ.ቁ | ክልል | ደረጃ ሶስት | ደረጃ ሁለት | ደረጃ አንድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | 1617 | 1365 | 1204 |
| 2 | አዳማ ከተማ | 1607 | 1386 | 1236 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 1670 | 1418 | 1257 |
| 4 | አዲስ አበባ | 2534 | 1922 | 1638 |
| 5 | ሲዳማ | 1670 | 1418 | 1257 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1456 | 1285 | 1148 |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ጋምቤላ | 1467 | 1285 | 1145 |
| 8 | ሀረሪ | 1628 | 1425 | 1278 |
| 9 | ሶማሌ | 1414 | 1236 | 1099 |
| 10 | አፋር | 1446 | 1264 | 1103 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 1670 | 1418 | 1257 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | 1628 | 1428 | 1285 |
| 13 | ትግራይ | 1638 | 1383 | 1218 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1670 | 1418 | 1257 |

ለ) ለዞን ዋና ከተማ በየክልሉ ለዞን ዋና ከተሞች የተመደበው ከታች በሠንጠረዥ 2 የተመለከተውን፤

**ሰንጠረዥ 2፡- የዞን ዋና ከተሞች የአበል መጠን**

| ተ.ቁ | ክልል | ደረጃ ሶስት | ደረጃ ሁለት | ደረጃ አንድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | 1432 | 1145 | 970 |
| 2 | ኦሮሚያ | 1407 | 1218 | 1078 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 1341 | 1138 | 991 |
| 4 | አዲስ አበባ | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ሲዳማ | 1341 | 1138 | 991 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1281 | 1089 | 945 |
| 7 | ጋምቤላ | 1355 | 1131 | 977 |
| 8 | ሀረሪ | 0 | 0 | 0 |
| 9 | ሶማሌ | 1323 | 1078 | 917 |
| 10 | አፋር | 1348 | 1127 | 991 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 1341 | 1138 | 991 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | 0 | 0 | 0 |
| 13 | ትግራይ | 1460 | 1155 | 977 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1341 | 1138 | 991 |

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ሐ) በወረዳ ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዋና ከተሞች ከታች በሠንጠረዥ 3 የተመላከተውን ይከፈላል::

ሰንጠረዥ 3፡- የወረዳ ከተሞች እና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የአበል መጠን

| ተ.ቁ | ክልል | ደረጃ ሶስት | ደረጃ ሁለት | ደረጃ አንድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | 1190 | 1022 | 889 |
| 2 | ኦሮሚያ | 1271 | 1054 | 907 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 1187 | 1008 | 872 |
| 4 | አዲስ አበባ | | | |
| 5 | ሲዳማ | 1187 | 1008 | 872 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1061 | 931 | 809 |
| 7 | ጋምቤላ | 1148 | 959 | 819 |
| 8 | ሀረሪ | | | |
| 9 | ሶማሌ | 1131 | 963 | 830 |
| 10 | አፋር | 1236 | 1026 | 879 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 1187 | 1008 | 872 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | | | |
| 13 | ትግራይ | 1250 | 1176 | 935 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1187 | 1008 | 872 |

4. የገጠር ቀበሌ የቀን ውሎ አበል በደመወዝ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም የመንግስት ሠራተኛ 200 ብር ይከፈላል::

5. አንደንድ የክልልና የዞን ከተሞች ሆነው የወረዳ ከተማ መቀመጫዎች በሆኑበት ለክልሎች ወይም ለዞን ከተሞች የተመደበው የቀን ውሎ አበል ተመን ለወረዳው ከተማ ጭምር የሚያገለግል ይሆናል::

6. የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የብዝሀ ከተማ መርህ የሚከተሉ ስለሆነ የክልል ዋና ከተማ ቢሮዎች ያሉባቸዉ ከተሞች ተወስደዉ ለልክሎቹ ዋና ከተማ የተወሰነዉ የአበል መጠን ተፈፃሚ ይሆናል::

7. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመሠራት ላይ የለ የመንግሥት ሠራተኛ ቀድሞ በተያዘ እቅድ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውስጥ ለሥራ ተንቀሳቅሶ ለምሳ ወደ መደበኛ የሥራ ቦተው መመለስ

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

የማይችል ከሆና እቅዱ ለመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ሲጸድቅ ብቻ ለአዲስ አበባ ከተማ ከተፈቀደው የቀን ውሎ አበል በደመወዝ መጠኑ መሠረት 25% ለምሳ ይከፈለዋል።

8. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 5 ከተመለከተው በስተቀር መደበኛ የሥራ ቦታ የሚገኝበት የክልል ከተማ፣ የዞን ከተማ ወይም የወረዳ ከተማ ውስጥ በመዘዋወር ሥራውን ለሚያከናውን የመንግስት ሠራተኛ የውሎ ገብ አበል አይከፈለውም።
9. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ መሥሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የተሠጠው አገልግሎት ሂሳብ ከሚከፈለው የቀን ውሎ አበል ላይ ተቀናሽ ይሆናል።
10. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለ በኃላ አዲስ የሚደራጁ የዞን ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ሲኖሩ የቀን ውሎ አበል መጠኑ ቀድሞ ተደራጅቶበት ለነበረው የዞን ወይም ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የተመደበው የቀን ውሎ አበል መጠን ይኖራል።

## 7. የአየር ጠባይ አበል ወደ ሚከፈልበት የሥራ ቦታ ለሚላክ ሠራተኛ የሚከፈል የቀን ውሎ አበል

አንድ የመንግስት ሠራተኛ ለሥራ ጉዳይ የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ሲላክ፡-

1. በአንደኛ ደረጃ 40% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 40% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።
2. በሁለተኛ ደረጃ 30% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 30% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።
3. በሰስተኛ ደረጃ 20% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 20% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።

## 8. የቀን ውሎ አበል የሚከፈልበት የጊዜ ወሰን

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ተልኮ ያለመቋረጥ በመሥራት በአንድ ቦታ እስከ አንድ ወር የቆዬ እንደሆነ ለቆየባቸው ቀናት የቀን ውሎ አበል ይከፈለዋል። ሆኖም ሥራው ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ የሚቆይ

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

መሆኑ ሲረጋገጥ የመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ በተጨማሪ እስከ ሁለት ወር የአበል ክፍያ እንዲቀጥል ሊፈቅድ ይችላል::

2. አንድ የመንግስት ሠራተኛ ሥራው በፕሮግራም የተደገፈ ሆኖ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ተልኮ የሚቆይበት ጊዜ ከ 3 ወር በላይ የሚፈጅ መሆኑ በቅድሚያ ከተረጋገጠ እና በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ሠራተኛው የሥራ መደቡ ወደሚገኝበት ቦታ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353 አንቀፅ 53(2) እና አንቀጽ 54(1-4) መሠረት እንደስፈላጊነቱ እንዲዘዋወር ማድረግ ይቻላል::

3. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 8(2) ቢኖርም በሥራ በህሪያቸው አስገዳጅነት ከፌዴራልና ከክልል ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው በመራቅ ከ ሶስት ወር በላይ የሚቆዩ የመንግስት ሠራተኞች ሥራውን በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ባለሙያ መድበው ማስራት የማይቻል መሆኑ ከታመነበት እና በጀት አስቀድሞ መያዙ ሲረጋገጥ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሥራው እንዲጠናቀቅ የመስክ ቆይታ ጊዜውን ሊፈቅድ ይችላል::

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. ለቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅጾች

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠያቂያ፣ መክፋያና መፍቀጃ ቅፆች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል::
2. የቀን ውሎ አበል እንዲከፈል የጠየቀ የሥራ ኃላፊ በሠራተኛ የተሞላ ቅጽ በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣል::
3. የቀን ውሎ አበል እየተከፈለው ወደ ሌላ የሥራ ቦታ የተላካ የመንግስት ሠራተኛ ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የቀን ውሎ አበል መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ በመሙላት ስላከናወናቸው ሥራዎች መግከጫ እንዲያቀርብ ይደረጋል::
4. የቀን ውሎ አበል ክፍያ እንዲጸድቅለት የሚጠይቅ የሥራ ኃላፊ የመስክ ጉዞ ሪፖርት መቀበሉን የሚያረጋግጥ መግለጫ በማፅደቂያ ሰነዶች ላይ ማመልከት አለበት::
5. በአባሪነት የተካተቱት ሠንጠራዥች እና ቅጾች የመመሪያው አካል ናቸው::

### 10. የመንግስት ሀብትን በቁጠባ ስለመጠቀምና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች

1. በፌደራል ተቋማት፣ በሁሉም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በጀት በሚያዝበት ወቅት በአመቱ የመስክ ሥራ የሚመለከታቸው ሠራተኞች ተለይተው

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ለምን ያህል ቀናት እንደሚሰማሩ እቅድ መያዝ እና የተያዘውም በጀት ከፕሮግራም በጀት አሠራር ጋር እንዲተሳሰር ማድረግ ይገባል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጀት ዝግጅት ወቅት የመሥሪያ ቤቱ እቅድ ያልተካተተ ስራ ሆኖ ይህንኑ አለመከናወን በመሥሪያ ቤቱ የተልዕኮ አፈፃፀም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ሚችል ሲሆን፣ ችግሩን ሊያቃልል የሚችል እቅድ ቀርቦ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲፈቅድ ብቻ የመስክ ጉዞው እንዲከሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡
3. የመንግስት ሠራተኞች ለመስክ ሥራ እንዲሠማሩ ሲደረግ ለሥራ ከሚቆዩት ቀናት ውጪ የተጨማሪ ቀናት ትርፍ ክፍያ እንዳይፈጸም በፌደራል ገንዘብ ሚኒስቴርና በክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የገንዘብ ቢሮዎች አመካይነት በካሽ ፍሎው ማኔጅመንት ሂደት ላይ ተገቢው ክትትል ይደረጋል፡፡
4. በየበጀት አመቱ በመንግስት የውሎ አበል በጀት የሚሸፈን የመስክ ጉዞ ስምሪት ከ90 ቀናት እንዳይበልጥ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡
5. የውሎ አበል ክፍያ በፌደራልም ሆና በክልሎች የኦዲት መ/ቤቶች የስጋት ክትትልና ቁጥጥር ቅድምያ መስፈርት ሆኖ እየተሰራበት መሆኑ እንደለ ሆኖ ወደፊትም የውሎ አበል ክፍያና የመስክ ጉዞ ጉዳይ ዋናው የኦዲት ትኩረት መስክ እንዲሆን በማድረግ የቁጥጥር ሥርዓት መጠናከር አለበት፡፡

## 11. ስለተሻሩ መመሪያዎች

1. በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በየካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ሲስኮ/ኮቢ/2014/1 ተላልፎ በሥራ ላይ ያለው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል ሰርኩላሮችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 12. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለኮሚሽኑ እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

Civil Service Commission
Federal Democratic Republic of Ethiopia

13. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው በኮሚሽኑ እየታየ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ሊሻሻል ይችላል፡፡

14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድህረ ገጽ ከተጫነ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም 2018

መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር)

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር

## አባሪ

<u>ቅጽ 1</u>

### የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ

| ተ.ቁ | የቀን ውሎ አበል መጠየቂያና መፈቀጃ | | የክፍያ አይነት | የክፍያ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተቋም ስም | | በቅድሚያ የተከፈላ | |
| 2 | የፕሮግራም/የሥራ ሂደት | | ለውሎ አበል ብር | |
| 3 | የፕሮጀክት ስምና ኮድ | | ለአየር ፀባይ አበል | |
| 4 | የጉዞ ዓለማ/ምክንያት | | ለነዳጅ/ቅባት ብር | |
| 5 | የጉዞው መነሻ | | ለመጠባበቂ ብር | |
| 6 | የጉዞው መድረሻ | | በጠቅላለ የተከፈላ | |

የሠራተኛው ስም---------------------------------- የሥራ ኃላፊ ሥም-------------

ፊርማ-------------------------------------------- ፊርማ-----------------------

ሂሳቡን የረጋገጣው ስም---------------------------------------------

ፊርማ------------------------------------------- የተቋሙ ማህተም

ግልባጭ:-

- ለፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት

ቅጽ 2

## የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መፍቀጃ ቅጽ

1. የመሥሪያቤቱ ሥም-----------------------------------------
2. የፕሮግራም/የሥራ ሂደት----------------------------------
3. የሠራተኛው ሥም------------------------------------------
4. የደመወዝ መጠን-----------------------------------------
5. የመጓጓዣ አይነት------------------------------------------
6. የውሎ አበል አከፋፈል ስሌት ሠንጠረዥ

ሀ) ሠራተኛው በጉዞ ላይ የቆየበት ቦታዎች (ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለዕራት) መግለጫ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | መነሻ | | | የደረሰበት ቦታ | | | | በፋይናንስ ባለሙያ ብቻ የሚሞላ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቦታ | ቀን | ሰዓት | ቀን | ቁርስ | ምሳ | ዕራት | የቀን ብዛት | የውሎ አበል መጠን | የአየር ጠባይ አበል | ድምር |
| 1 | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | ድምር | | | |

ለ) ሠራተኛው ለሥራ የቆየባቸው ቦታዎች መግለጫ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቀን | ለሥራ የታደረበት ቦታ ክልል/ዞን/ወረዳ/ከተማ | የቀን ብዛት | በፋይናንስ ባለሙያ ብቻ የሚሞላ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የውሎ አበል | የበረሃ አበል | ድምር |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ሐ) አጠቃላይ የውሎ አበልና ነዳጅ ክፍያ ማጠቃለያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የክፍያ አይነት | ቅድሚያ የተከፈለ የገንዘብ መጠን | ተጨማሪ ክፍያ | ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ መጠን | ድምር/ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የውሎ አበል | | | | |
| 2 | የነዳጅ | | | | |
| 3 | የጥገና | | | | |
| 4 | ሌላ | | | | |
| | ጠቅላላ ወጪ | | | | |

የሠራተኛው ስም-------------------------

ፊርማ-----------------------------------

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም ----------------

ፊርማ-----------------------------------

ሂሳቡን የዘጋጀው ሠራተኛ ስም ---------

ፊርማ-----------------------------------

ሂሳቡን ያረጋገጠው ኃላፊ ስም------------

ፊርማ-----------------------------------